ዴሞክራሲያ

****************************************************
* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሣን*
****************************************************

ቅጽ 34 ቁጥር 1 ኅዳር 2001 ዓ. ም.

# ለወቅታዊ አንገብጋቢና መሰረታዊ ችግራችን ዘላቂ አፋጣኝና ተገቢ ምላሻችን

“ንብ ባውራው፥ ገበሬ ባዝመራው ይታወቃል” እንዲሉ ድርጅታችን ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት ከደረሰበት ጭቆና ላንዴና ለመጨረሻ ሊገላገል የሚችለው በነፃና ፍትሓዊ ምርጫ የሕዝብ ይሁንታን ያገኘ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሲመሰረት ብቻ መሆኑን ደጋግሞ ግልፅ አድርጓል፡፡ ለዚህም ነው “ዴሞክራሲ ያለገደብ”፤ “ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም”፤ የሚሉ ዓቢይና ወቅታዊ መፈክሮችን በቀዳሚነት አንግቦ የደምና የአጥንት ዋጋ ጭምር ከፍሎ የሕዝብ ወገንተኝነቱን በተግባር እያረጋገጠ ዛሬም ድረስ በትግሉ የቀጠለው፡፡ ይህንን እውነት አሌ ሲሉ የኖሩት ታድያ ማሩን አምርሮ ወተቱን አጥቁሮ እያሉ በሕዝብ ደምና አጥንት እያላገጡ ያሉት የዛሬው ህወሓት/ኢሕአዴግና ለጅብ አፍ ዳርገውን ያለፉት የትናንት ጨቋኝ ገዥዎቻችን ብቻ ናቸው፡፡ ዛሬ ሃገራችንም ሆነች ሕዝቧ መንስዔያቸው ውስጣዊና ውጫዊ በሆኑ ከባድ ከባድ ችግሮች ተወጥረውና ለከፍተኛ ብሔራዊ አደጋ ተጋልጠው ለመገኘታቸው እማኝ መጥራት አያሻንም፡፡ ዓይኔን ግንባር ያርገው ከሚሉ ጥቂት የገዢው አሸባሪና ዘረኛ ቡድን አባላትና ጋሻ ጃግሬዎች በስተቀር በሃገራችን ውስጥ የኢኮኖሚ ድቀት ስር ሰድዶ፥ የሸቀጥና ምርት ዋጋ ንሮ፥ ስራ አጥነት ጣሪያ ነክቶና የማኅበራዊ ኑሮ ግልጋሎቶች ተመናምነውና ጠፍተው፤ ይኸው ሕዝባችን ለከፍተኛ የረሃብ አደጋ መጋለጡ ሊደበቅ የማይችል ያፈጠጠ ዕውነት ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡

ህወሓት ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮም ፀረ-ኢትዮጵያ ነበርና ኢሕአዴግ የሚለውን ጭምብል ካጠለቀም በኋላ በሃገር ውስጥ በዘርና በሃይማኖት ሕዝብን በመከፋፈል እኩይ ድርጊቱ ሳይገታ ቀጥሏል፡፡ይባስ ብሎ ዛሬ በጎረቤት ሃገር በሱማልያ እየፈፀመ ያለው ጣልቃ ገብነትና ወረራ ለለጣቂ ትውልድ የሚቆይ የማያባራ ጦስ ሊሆን እንደሚችል ቢመከር ቢዘከርም የአምባገነን ባሕርይው እያሸነፈው የጥፋት ተልዕኮውን በአይዞህ ባዮቹ የባዕድ ሃገር መሪዎች እየታገዘ ቀጥሎበታል፡፡ ህወሓት/ኢሕአዴግ በቅርቡ በምዕራቡ የሃገራችን ክፍል ከጎንደር እስከ ኢሊባቦር (ጋምቤላ) የሚደርሰውን ለም መሬት ቆርሶ ለሱዳን አሳልፎ በመስጠት ታላቅ ብሔራዊ የክህደት ተግባር ተሰማርቶ ከማይወጣው አጣብቂኝ ውስጥ ገብቷል። በሀገሩ ጉዳይ ሁሌም ቀናዒ የሆነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከማስቆጣት አልፎ ሁኔታው እየተባባሰ መጥቶ ወደመሳሪያ ግጭት ሊያመራ እንደሚችል በቀላሉ መገመት ይቻላል፡፡ እኒህ ፍፁም ሃላፊነትና አስተዋይነት የጎደላቸው ነግ ከነግ በስቲያ ኢትዮጵያውያን ከአጎራባች ሃገሮች ሕዝቦች ጋር በሰላምና በወዳጅነት ተከባብረው እንዳይኖሩ የሚያግዱና ሆን ተብለው በህወሓት/ኢሕአዴግ የሚጎነጎኑ ፀረ ሕዝብ ድርጊቶች የስርዓቱን ፀረ-ኢትዮጵያ መሰሪ ዓላማ

እጅጉን አጉልተው የሚያሳዩ ነጸብራቆች ናቸው:: ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ለዚህ መሰሪ ተግባር በጥሞና የተጠና መፍትሄም ሊሹለት የሚገባ ታላቅ አገራዊ ጉዳይ ነው::

ህወሓት/ኢሕአዴግ በሱማሊያ ውስጥ በሚያካሄደው ወረራና ጭፍጨፋ ምክንያት አካባቢያዊ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ አገሮችና መንግስቶች አገራችንና ሕዝቧን በመጥላት ዓላማና ግባቸው በውል ወደማይታወቁ የጦርነት አደጋዎች እንዳይገፉን ጥንቃቄ ማድረግ የሚኖርብን ዛሬ እንጂ ነገ አይደለም:: በሌላ በኩል ደግሞ፥ ምንም እንኳን የዘንድሮው የአሜሪካ የፕሬዚዳንት ምርጫ ውጤት በምንም መልኩ ቢታይ ታሪካዊ ከመሆኑም በላይ ለወደፊቱ የዓለም ሁኔታ ትልቅ ተስፋ ሰጪ ቢሆንም፥ የአሜሪካ መንግስት ለህወሓት/ኢሕአዴግ የሚያደርገው ገደብ የለሽ ሁለንተናዊ ድጋፍ ባጭር ጊዜ ውስጥ ካልተለወጠ የድጋፉ ቀጣይነት በኢትዮጵያ የተቃዋሚ ሃይሎች እንቅስቃሴ ላይ የሚፈጥረውን መሰናክል ካሁኑ መገመት አያዳግትም:: በዚህም ላይ ተጨምሮ የሻዕቢያ የቆየ ፀረ-ኢትዮጵያ እርምጃዎችና ፖሊሲዎች ለሃገራችን ህዝብና ለተቃዋሚ ድርጅቶች ትግል አሉታዊ እንደሚሆኑ ማወቅ ያስፈልጋል:: የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ የሚሆነውና አጥጋቢ መልስ የሚሻው ታድያ ከተደቀኑብን አሉታዊ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮቻችን ለመውጣት ምን መደረግ አለበት? የሚለው ይሆናል::

ለዚህ መሰረታዊ ጥያቄ የኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ቀዳሚ ምላሽ የህወሓት/ኢሕአዴግ የፖለቲካ ስርዓት መወገድ የሕዝባዊ ትግሉ ስትራቴጂያዊ ግብ መሆኑ በሁሉም የተቃዋሚ ኃይሎች ዘንድ ግልጥነት ሊያገኝ ይገባል የሚል ነው:: በድርጅታችን ፕሮግራምና በዋና ዋና ድርጅታዊ ልሳኖቻችን ላይ ተደጋግሞ በግልፅ እንደተጠቆመው ህወሓት/ኢሕአዴግ ለኢትዮጵያ በጎ የሚመኝና ሕዝቦቿን በአኩል ዓይን የሚያይ ድርጅትና መንግስት አይደለም:: ቀደም ሲልም ሆነ በምርጫ ዘጠና ሰባት ማግስት በግልጥ እንደታየው ህወሓት/ኢሕአዴግ በምርጫና በሰላማዊ የስልጣን ሽግግርና መጋራት የሚያምን መንግስት አይደለም:: በተደጋጋሚ ድርጊቶቹ በግልጥ እንዳስመሰከረው ህወሓት/ኢሕአዴግ በአገሪቱ ውስጥ ሰላምና የተረጋጋ ኑሮ እንዲኖር የሚፈልግ መንግስት አይደለም:: አሸባሪ፥ ጠብ ጫሪና ለቀጣይ ትውልድ ጭምር ቂምና በቀል የሚያተርፍ ሃላፊነት የሚጎድለው አገዛዝ ነው:: ስለሆነም ህወሓት/ኢሕአዴግ ስልጣን ላይ አስካለ ድረስ አገሪቱ ከገባችበት አዘቅት ልትወጣ እንደማትችል በፅኑ ማመን ቀዳሚ ጉዳይ ነው:: በዚህ ስትራቴጂያዊ ግብ ላይ ብዥታ መኖር የዋህነት ብቻ ሳይሆን የትግሉንም ግብና አቅጣጫ እንደ መሳት ይቆጠራል:: ስለዚህ፥ ከምንም ነገር በፊት ሁሉም ተቃዋሚ ኃይል ሊገነዘበውና በእርግጠኝነት ሊያምንበት የሚገባው ዋነኛው ቁምነገር የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግስትና የፖለቲካ ስርዐቱ ጨርሶ መወገድን መሆን አለበት::

እምነትና አቋም መውሰድ ብቻ ሳይሆን በእርግጥም የህወሓት/ኢሕአዴግን መንግስትና የፖለቲካ ስርዓት ለማስወገድ የሚደረገው የትግል ስልት ዘዴና ደረጃ ይጠይቃል:: ዋነኛውና ተቀዳሚው ጉዳይ ወሳኙ ትግል የሚካሄደው በአገሪቱ በኢትዮጵያ ውስጥ፣ በኢትዮጵያኖች ድጋፍና ተሳትፎ ብቻ መሆኑን ማመንና መቀበል ይሆናል:: ከአገሪቱ ውጭ ያሉት ኢትዮጵያኖችና ድርጅቶች ተሳትፎ የአገር ቤቱን ትግል ከመደገፍ የማያልፍ መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል:: በውጭ የሚገኘው ሃይል ሙሉ የድጋፍ ትኩረቱ ለአገር ቤቱ ትግል መሆን እንዳለበት በተግባር ማሳዬቱና ዘዴውንም መጠቆሙ ሳይውል ሳያድር መጀመር አለበት:: ቀደም ሲል ይደረጉ የነበሩትን በጥሞና መርምሮ አሉታዊውን ከአዎንታዊው እያነፃፀሩ በጎውን ተቀብሎ ወደፊት ለመራመድ ቁርጠኛ ዝግጁነት እንዲኖር ጊዜው ግድ ይላል::

የትግሉን ዘዴ የሚወስኑት ጉዳዮች በአገሪቱ ውስጥ በጉልበት የተንሰራፋው መንግስት ጠባዮችና የሕዝቡ ፍላጎቶችና ዝግጅቶች ናቸው:: የህወሓት/ኢሕአዴግን የአስራ ስምንት ዓመታት ፍፁም አምባገነን አገዛዝ በጥሞና ለተከታተለና ላጤነ ሁለ-ገብ የትግል ስልት ዛሬም ትክክለኛው የትግል ዘይቤ መሆኑ አይሳተውም:: ይህ አጠቃለይ የትግል ስልት

ማንኛውንም ነጠላ የትግል ስልት አይኮንንም፥ አያበላልጥም፥ እንደተደጋጋፊ እንጂ እንደተቃራኒ አይመለከትም። ማንኛውም ድርጅት ሕዝባዊውን ትግል ለማገዝ የራሱን ድርጅታዊ ይዞታና ችሎታ አመዛዝኖ የሚወስነውን የትግል ስልት ማንኛውም ሌላ ድርጅት ሊያወግዘው ቀርቶ ሊቃረነው አይገባም፥ አይችልም። ዋናው ቁምነገር፥ ድርጅቱ ከአጠቃላዩ የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ትግል አንጻር፥ በህወሓት/ኢሕአዴግ መንግስትና የፖለቲካ ስርዓቱ መወገድ አጥብቆ የሚያምንና ለተግባራዊነቱም ዝግጁ ሆኖ መገኘቱ ብቻ ነው።

የተቃዋሚ ድርጅቶች ዋነኛውን የብሔራዊ ትግሉን ዓላማ፥ ማለትም የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግስትና የፖለቲካ ስርዓት መወገድ፥ ለማስቻል በየደረጃው የሚከተሏቸው ታክቲካዊ የፖለቲካ ውሳኔዎችና እርምጃዎች በየዕለቱ አገሪቱ ውስጥ የሚከሰቱትን ፖለቲካዊ እውነታዎች ያገናዘቡና በተቃዋሚ ኃይሎች መካከል ስምምነትን የሚያስገኙ መሆን ይኖርባቸዋል። ለዚህ በየአምስት ዓመቱ ህወሓት/ኢሕአዴግ የሚያደርገው አገራዊ ምርጫ አንዱ ምሳሌ ነው። ድርጅቶች በዚህ ምርጫ ውስጥ እንሳተፋለን ብለው ሲወስኑ፥ ከላይ የተጠቀሱት የህወሓት/ኢሕአዴግ ጠባዮች ከግምት ውስጥ እንዳሉ፥ ምን ለማስገኘት እንደሆነ በቅድሚያ ለራሳቸው ግልጥ መሆን ይኖርባቸዋል፥ ከትግል አጋሮቻቸውም ጋር ስምምነት ሊኖራቸው ይገባል። በየጊዜው የሚወሰዱት ታክቲካዊ የፖለቲካ ውሳኔዎችና እርምጃዎች ስትራቴጂያዊ የትግሉን ዓላማና ግብ የሚያራምዱ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) የብሄራዊ ዴሞክራሲያው ትግሉን በተሳካና አስተማማኝ በሆነ መልኩ ለማካሄድ፥ ለጥቆም የተረጋጋና ሁሉን አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግስት ለመመስረት፥ ከዚያም ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ የሁሉም የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅቶች ኅብረት መፈጠር ወሳኝ መሆኑን አጥብቆ ያምናል። እርግጥ ነው፤ ኅብረት ምስረታ ብዙ ግዜ የተለፈፈለትና የተሞከረ ቢሆንም፥ ከአንግዲህ ወዲህ የሚፈጠረው ኅብረት ካለፉት ውድቀቶች የተማረና የወደፊቱን በጥናትና በምክክር ላይ ያስመረኮዘ ማድረግ ያስፈልጋል። በአንድ በኩል፥ አገሪቱ በየሰዓቱ እየደማችና ሕዝቧ እየረገፈ መሆኑን በውል መገንዘብና፥ በሌላ በኩል ደግሞ የኅብረት ትግል ምርጫ ሳይሆን ብሄራዊ ግዴታ መሆኑን ማመንና መቀበል ከሁሉም ለአገር አሳቢ ድርጅቶች ይጠበቃል።

በዛሬው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ብቻውን ታግሎ ኢትዮጵያን ከህወሓት/ኢሕአዴግ አምባገነን አገዛዝ ነጻ የሚያደርግ ድርጅት የለም። ጉልህ በሆነ መልኩ በትግል ላይ ካሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ጎልብቶ የድርጅቶችን እምነትና ክብር የተጎናጸፈ ድርጅት የለም። ፍላጎቱን ብቻ በሌሎች ድርጅቶች ላይ ለመጫን የሚችልም ድርጅት የለም፥ ካለም አይፈቀድለትም፥ ተገቢም አይደለም። በፀረ-ህወሓት/ኢሕአዴግ ትግል ላይ የራሱን አስተዋጽዖ ለማበርከት በሀቅ ከተሰለፈ ደግሞ የሚናቅና የሚገለል ኢትዮጵያዊ ድርጅት አይኖርም። ስለዚህ፥ መፈጠር ያለበት የድርጅቶች ኅብረት ሁሉን አቃፊና አሰባሳቢ እንጂ አግላይ ሊሆን አይገባም፥ አይችልም። ማንኛውም ድርጅት እንዲፈጠር የሚፈለገውን ኅብረት መሰረታዊ የመሰባሰቢያ እምነቶች እስከተቀበለ ድረስ ከኅብረቱ ድንኳን ውጭ ሊሆንም አይገባም።

በኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ፅኑ እምነት የኅብረቱ መሰረታዊ የመሰባሰቢያ እምነቶች ሦስት ናቸው፥ (1) የኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነትና ብሄራዊ ሉዓላዊነት፥ እንዲሁም በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የሕዝቧ አንድነት (2) የሁለንተናዊ የሕዝቧ የዜግነት መብቶች (ማለትም የኤኮኖሚ የፖለቲካ የማኅበራዊና የሰብዓዊ መብቶች) መከበርና የመድብለ-ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መመስረትና (3) የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግስትና የፖለቲካ ስርዓት መወገድ ናቸው። ሶስቱ መሰረታዊና አጠቃላይ እምነቶች ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ዝርዝር የፖለቲካ ፍላጎቶች በላይ ናቸው። እነኝህ ሶስት እምነቶች የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ለሚታገሉ ድርጅት ትብብርና ግንኙነት ቀዳሚ መሰረቶች ናቸው።

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ሌላው ዓቢይ ቁምነገር ስለ ኅብረት ሰርክ መለፈፍ ወይም ስለኅብረት ጠቃሚነት ነጋ ጠባ ማውራቱ በራሱ ህብረትን እውን ሊያደርግ አለመቻሉ ነው። ቢያንስ ካለፈው የረጅም ዘመን የትግል ተመክሮ መለስ ብሎ መቃኘትና ጠቃሚ ትምህርት ለመቅሰም ድፍረቱን ሊኖረን ይገባል። እንደሚታወቀው የተለያዩ የህብረት ጥረቶች ተሞክረዋል፥ ኅብረቶችም ተመስርተዋል። የተመሰረቱት ኅብረቶች ድክመቶችና ጥንካሬዎች ነበሯቸው፥ የተሳኩም ያልተሳኩም ይገኙባቸዋል። የፖለቲካ ትግል ሂደቱ አልጋ ባልጋ አይደለምና ድክመቶች ድርጅቶችን ከትግል ሊያቅቡ ወይም አለመሳካቶች በሕዝባዊ ትግሉ ቀጣይ ባሕርያት ላይ ጳመና እንዲጥሉ ጨርሶ መፈቀድ የለበትም። ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬም የመፍትሄ ያለህ ጩኸታቸው አላቆመምና!! የዚያኑ ያሕል በኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች የትግል ታሪክ ሂደትም ቀናና ጠመዝማዛ ጎዳናዎች ታልፈው ነበርና ዛሬ ከደረሱበት ምዕራፍ ላይ ሆኖ ትናንትን እያሻቀቡ በመመልከት አርአያነታቸውንና በጎ ጥረታቸውን ገሸሽ በማድረግ የገጠሟቸውን መሰናክሎች መኮነን ላይ ብቻ ማትኮሩ በራሱ ፋይዳ አይኖረውም። ለአብነት ለመጥቀስ ያህል በቅርቡ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ዓቢይ የሚባሉ ድርጅቶች ውስጣዊ መከፋፈል ደርሶባቸው አስተውለናል። እነኝህ መከፋፈሎች በራሳቸው መጥፎነት የላቸውም። በአንድ ድርጅት ውሰጥ ሆነው በመተራመስና በመጠላለፍ አመርቂ ስራዎችን መስራት ካልቻሉባቸው ሁኔታዎች ወጥተው በተሻለ አሰራርና አወቃቀር ራሳቸውን በበቂ በማደራጀት ከላይ በተጠቀሱት መሰረታዊ እምነቶች ላይ መስማማትን ፈጥረው በጋራ የኅብረት ትግል ላይ ዳግም ለመገናኘት ከቻሉ እሰየው። ይህንን ለማስቻልም ሁሉም በየግላቸው በአንድ በኩል ውስጣዊ መደላደሎችን እያደረጉ በሌላ በኩል ደግሞ ለህዝቡ የየራሳቸውን ራዕዮች እያሳዩ በመሰረታዊ የጋራ እምነቶች ላይ ሊተባበሩ እንደሚችሉ እየገለጹ ለመቆዬት መቻል ይጠበቅባቸዋል። ስድብና እሽኮለሌ መግጠሙ አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ ከግምት ውስጥ የሚጥልና ቆምንለት ለሚሉት ሕዝብ ትግልም ቅንጣት ታህል አስተዋፅኦ እንደማያደርግ በገሃድ ታይቷል።

ይልቁንም ባሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅቶች በጋራ ወይም በተናጠል በመነጋገርና በመቀራረብ የኅብረት ምስረታውን ሂደት ካሁኑ መጀመር ይጠበቅባቸዋል። ሆኖም ግን፥ ይህ ሂደት ለፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ የሚተው ሳይሆን አገር ወዳድ ዜጎችንና የሲቪክ ማኅበረ ሰቦችንም የሚያጠቃልልና የሚያሳትፍ መሆን ይኖርበታል። የኅብረት ምስረታውን ሂደት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ባለቤትነት ሊይዘው ይገባል። ሕዝቡና የሲቪክ ማኅበረ ሰቦችም ይህንን የኅብረት ምስረታ ሂደት ሊቆጣቋሩና ሊያግዙ የሚችሉት ንቁና ቆራጥ ተሳትፎ ለማሳዬት ሲችሉ ብቻ ነው። ይህም ማለት የኅብረት ምስረታውን ሂደት የሚንከባከቡትንና የሚያራምዱትን ድርጅቶች በገንዘብ በሞራልና በተግባር እያገዙና እያበረታቱ፥ ለኅብረቱ ምስረታ እንቅፋት የሚሆኑትን ግን እያጋለጡ እያራቁና እያወገዙ ለመሄድ መቻል ይኖርባቸዋል ማለት ነው። ከዳር ቆሞ ተመልካችነት አደናቃፊዎቹን ከማበረታታቱም በላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ መከራንና ሰቆቃ እንደማራዘም ይቆጠራል። በአገራችንና በሕዝባችን ላይ እያንዣበቡ ያሉት አደጋዎች የጠቅላላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንጂ የጥቂት ግለሰቦችና የፖለቲካ ድርጅቶች ጉዳይና ጣጣ አይደሉም። ስለዚህ፥ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ንቁ ተሳትፎ ከምን ጊዜውም በበለጠ ደረጃ ይፈለጋል።

ይህንን የኅብረት ምስረታ ሂደት ለማስጀመር መቀራረብና መግባባት የሚያሳዩ ድርጅቶች በሚመቹአቸው መንገዶችና ዘዴዎች ከአሁኑ ውይይቱን ጀምረው በየደረጃው የተቀሩትን በማካተት ሁኔታው ሲበስልና ሲመች ሁሉን አቀፍ ጉባዔ በመጥራት ኅብረቱን ለመፍጠርና ለማወጅ መቻል ይኖርባቸዋል። ይህ እስኪረጋገጥ ድረስ በዋና ዋና የአገሪቱ ጉዳዮች ላይ ሰፋና ጠለቅ ያሉ ዝግና ይፋ ስብሰባዎች በነጠላና በጋራ እያካሄዱ ከአባላቶቻቻው ከደጋፊዎቻቸውና ከጠቅላላው ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ዜጋዎች ጋር መመካከርና ልዩ ልዩ ጥናቶች እንዲደረጉ መርዳትና ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል። ኢትዮጵያዊ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ለወቅታዊው ለአንገጋቢውና ለመሰረታዊው የህብረት ትግል ዕውን

መሆን አጥብቀው መታገል ያለባቸውን ያህል ኅብረቱ እስኪመሰረት ድረስ በተለያዩ ወቅታዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይም በጋራና በተናጠል ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይገባቸዋል።

አሸባሪው ዘረኛውና አምባገነኑ የህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ቀን እየቀጠረ በሚያመጣው፥ በሎሌነት ያደረላቸውን የባሕር ማዶ ጌቶቹን ጭምር በሚያታልልበትና ሁሉንም ነገር ሙሉ በሙሉ በራሱ ቁጥጥር ስር በሚያደርግበት የ2002 ምርጫ ጉዳይ ላይ ሽር ጉድ ማለቱን ጀምሯል። የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች አቋም በዚህ ላይ ምን መሆን ይኖርበታል? እንዴት አድርገው አንድ ዓይነት አቋም እንዲኖራቸው ለማድረግ ይቻላል? ህገ-ወጥ የተባሉት ድርጅቶች ሚናቸው ምን መሆን አለበት? ህጋዊ ሆነው በህቅ የሚታገሉትን እንዴት አድርጎ ለመርዳት ይቻላል? ህወሓት/ኢሕአዴግ በዚህ ምርጫ አማካይነት ሌላ የአምስት ዓመት ዕድሜ እንዳይገዛ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ እንዴት አድርጎ ህጋዊነት እንዳያጣ ለማድረግ ይቻላል? እና ለመሳሰሉ ጥያቄዎች ካሁኑ በቂ መልስ መሻት ከኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅቶች ይጠበቃል። እነኝህንም መልሶችም ለማፍለቅ በድርጅቶች መሀል ካሁኑ መቀራረብና መነጋገር የግድ ይሆናል።

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ለወቅታዊው አንገብጋቢውና መሰረታዊው ችግራችን ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት የፖለቲካ ፍላጎቶች በላይ በሆኑት ሶስቱ የመሰባሰቢያ እምነቶች ላይ በመመርኮዝ ኅብረትን ዕውን ማድረግና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላቂ አፋጣኝና ተገቢ ምላሽ መስጠት አማራጭ የማይገኝለት ብሔራዊ ግዴታ መሆኑን በፅኑ ያምናል፤ ለተግባራዊነቱም አጥብቆ ይታገላል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!
የኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነትና ብሄራዊ ሉዓላዊነት በሕዝቧ አንድነት ተከብሮ ይኖራል!!
ብሄራዊ የዴሞክራሲ ትግላችን በኅብረት!!
ህወሓት/ኢሕአዴግንና የፖለቲካ ስርዓቱን ለማስወገድ በኅብረት እንታገል!!